የሰ/መ/ቁ. 69921

ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** አቶ አበበ ገ/እግዚአብሔር ጠበቃ ዮሐንስ ዘለቀ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** አራዳ ክፍለ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ዐቃቤ ህግ ተወዳጅ ሲማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ አስተዳደር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፤ የአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የንግድ ሥራ ገቢ ግብርን የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ አመልካች የ2000 ዓ.ም የበጀት ዘመን ብር 472,594.89 /አራት መቶ ሰባ ሁለት ሺህ አምሥት መቶ ዘጠና አራት ብር ከሰማኒያ ዘጠኝ ሣንቲም/ ያልተጣራ ትርፍ ያገኘ መሆኑን የሚያሣይ የሒሣብ መዝገብ አቅርቦ ብር 83,507.02 /ሰማኒያ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ሰባት ብር ከዜሮ ሁለት ሣንቲም/ የንግድ ሥራ ከፍሏል፡፡ ተጠሪ አመልካች በአመቱ ውስጥ ያገኙት ጠቅላላ ገቢ ብር 5,647,298.90 /አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ሥምንት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ መሆኑን አመልካች ያቀረበው የሂሣብ መዝገብ የሚያሣይ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ አመልካች የተሠማራበት የፅሕፈት መሣሪያ አስመጭነት ሥራ ዘርፍ ዕቃዎች የጉምሩክ ፎርማሊቲ አሟልተው ከገቡበት አሥራ አምስት ፐርሰንት ያልተጣራ ትርፍ የሚገኝ መሆኑ በአዲስ አበባ አስተዳደር ገቢዎች የተጠና ጥናትና የተዘጋጀ ቼክ ሊስት ያለ መሆኑን በመግለፅ በዚሁ ስሌት አመልካች ብር 303,610.71 / ሶስት መቶ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ አስር ብር ከሰባ አንድ ሣንቲም /ያልተጣራ ትርፍ ስላለ በዚሁ ስሌት ግብር እንዲከፍል የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ተጠሪ ለአመልካች ሰጥቷል፡፡

አመልካች ተጠሪ በሰጠው የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርቧል፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ የሰጠውን የገቢ ግብር ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለአዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርበው አቤቱታቸው ተቀባይነት አልተገኘም፡፡

አመልካች ሰኔ 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች ያቀረብኩት የሂሣብ መዝገብ የዋጋ ማሣነስ ወይም underinvocing የሌለው ነው፡፡ አመልካች የሒሣብ መዝገቡን ተቀብሎታል፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ ተጨማሪ ግብር እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 286/94 ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጥቅምት 14 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ለሰበር አቤቱታ በሰጠው መልስ ተጠሪ አመልካች ባቀረቡት የሒሣብ መዝገብ ላይ ያሉትን ጥቃቅን ስህተቶች በማረም ውሣኔ የሰጠው የአዋጅ ቁጥር 286/94 ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በመሆኑ የፈፀመው መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ተጠሪ ቀደም ብሎ በተዘጋጀ መመሪያና ቼክ ሊስት መሠረት በማድረግ አመልካች ተጨማሪ ግብር እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪ ያቀረብኩትን የሒሣብ መዝገብ ከተቀበለ በኋላ በተሰማራሁበት የፅሕፈት መሣሪያዎች አስመጭነት ንግድ ዘርፍ ሊገኝ ይችላል ተብሎ በግምት የተዘጋጁ የትርፍ ተመን መሠረት የግብር ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ተከራክረዋል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 69/1/ ግብር ከፋዩ ምንም አይነት የሂሣብ መዝገብና ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሣብ መዝገቡንና ሰነዱን የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ወይም ግብር ከፋዩ በዚህ ህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላሣወቀ እንደሆነ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን የግብሩን ልክ በግምት ሊወስን ይችላል በማለት ይደግጋል፡፡ ተጠሪ አመልካች በዓመት ውስጥ አስገብቸዋለሁ በማለት በሒሣብ መዝገብ ያሣወቀውን ብር 5,647,298.90 እና ሌሎች የወጪ መግለጫዎች የተቀበለ መሆኑ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ባቀረበው ክርክር አረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በበጀት ዓመቱ አግኝቻለሁ በማለት መግለጫ ያቀረበበት ያልተጣራ ትርፍ በዘርፉ ይገኛል ተብሎ በጥናት ከተረጋገጠው እና በመመሪያ ከተወሰነው አማካኝ ያልተጣራ ትርፍ በታች መሆኑን በማገናዘብ ይህንን የሒሣብ ስህተት በማስተካከል የግብር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ የአመልካችን የሒሣብ መዝገብ በከፊል በመቀበልና በከፊል በማስተካከል አመልካች ተጨማሪ የገቢ ግብር እንዲከፍል መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 71 ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት መንፈስና ዓላማ ጋር የሚቃረን ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም የህጉ ድንጋጌ ተጠሪ አመልካች ያቀረበው የሒሣብ መዝገብ ሙሉ በሙሉ የማይቀበልበት በቂ ምክንያት ካገኘ የአመልካችን የሒሣብ መዝገብ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ግብሩን በግምት የመወሰን ሥልጣን ለተጠሪ ይሰጠዋል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካች ያቀረበው የሒሣብ መዝገብ በከፊል ተቀባይነት ያላቸው የሒሣብ መግለጫዎችን የያዘ በከፊል ደግሞ የሒሣብ አያያዝና የአሠራር ስህተት ያለበት ሆኖ ቢገኝ ተጠሪ በሂሣብ አያያዝ የተፈጠሩ ስህተቶችን በማስተካከል የግብር ውሣኔ ከመስጠት የአዋጅ አንቀፅ 69 ድንጋጌዎች የሚገድቡ /የሚከለክሉ/ አይደሉም፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመዝነው ተጠሪ አመልካች በ2000 ዓ.ም የበጀት ዓመት የፅህፈት መሣሪያዎችን በማስመጣት ስላገኘው ጠቅላላ ገቢና ስለሌሎች ወጭዎች ያቀረበውን የሂሣብ መግለጫ ተቀብሏል፡፡ ሆኖም አመልካች በበጀት ዓመቱ ወደ አገር ውስጥ ያስገባውን የፅሕፈት መሳሪያ በመሸጥ አግኝቸዋለሁ ብሎ በሒሣብ መዝገቡ መዝግቦ የያዘው ያልተጣራ ትርፍ የፅሕፈት መሣሪያዎችን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት እንደሚገኝ በጥናት ተለይቶ ከተያዘው አማካኝ ያልተጣራ የትርፍ መጠን ዝቅተኛ ሆኖ በመገኘቱ አመልካች በዓመት ውስጥ ስላገኘው ያልተጣራ ትርፍ ሠርቶ ያቀረበውን የሂሣብ መግለጫ ተጠሪ ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው ብሎ አልተቀበለውም፡፡ ስለሆነም ያልተጠራ የትርፍ መጠን ለመወሰን የወጣውን መመሪያና ቼክ ሊስት መሠረት በማድረግ የአመልካችን ያልተጣራ የትርፍ መጠን የሒሣብ መግለጫ በማስተካከል አመልካች ተጨማሪ የገቢ ግብር እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 69 ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለው ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

- የአዲስ አበባ ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፤ የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡

  መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ